










# Just the fax



## የመጀመሪያው ዓመታዊ የምሥራቅ ኮልፋክስ የባህል ዲስትሪክት የማህበረሰብ የመስክ ቀን




ቅዳሜ ጁን 8 ቀን የመጀመሪያው የምስራቅ ኮልፋክስ የባህል ዲስትሪክት የማህበረሰብ የመስክ ቀን ተካሂዷል። በምሥራቅ ኮልፋክስ የባህል ዲስትሪክት አስተባባሪ ኮሚቴ ሀሳብ አመንጪነት እና ከThe Fax አጋርነት ጋር በመተባበር የተዘጋጀው የመስክ ቀን የማህበረሰብ አባላትን በማገናኘት የከተማው የንግድ ተቋማት (ቢዝነሶች) እንዲተዋወቁ እና ሰዎች እንዲንቀላቀሉ አድርጓል! እንደ አዲስ በተከፈተው "Mosaic" የማኅበረሰብ ካምፓስ (በቀድሞ ስሙ ጆንሰን እና ዌልስ ዩኒቨርሲቲ) የተካሄደው የመጀመሪያው የቤት ውጪ ዝግጅት ነበር።

የምሥራቅ ኮልፋክስ የባህል ዲስትሪክት አስተባባሪ ኮሚቴ የተዋቀረው በ2023 መገባደጃ ላይ ሲሆን የባህል ዲስትሪክት ዝግጅቶችን ለማዘጋጀት የሚሠሩ በአካባቢው ነዋሪዎችን እና የንግድ ተቋማትን (ቢዝነስ ባለቤቶችን) ያካተተ ነው። የባህል ዲስትሪክቱ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ጥቂት ዝግጅቶችን አድርጓል፣ ነገር ግን ከ200 በላይ ታዳሚዎችን በማራኪው ግቢ ያሰባሰበውን የመስክ ቀንን ያህል ትልቅ ዝግጅት ተደርጎ አያውቅም። ጎልማሶችን እና ልጆችን በአንድነት ለመማረክ በማሰብ የመስክ ቀኑ እንደ የጆንያ ሩጫ ውድድር፣ የውሃ ፊኛ መወራወር እና ሌሎችም የቆየት ያሉ የጨዋታ ዓነቶችን የአካተተ ነበር። ልጆች ሽልማቶችን የሚያስገኙ ኮከቦችን በመሰብሰብ ከእንቅስቃሴ ወደ እንቅስቃሴ ሲሯሯጡ፣ አዋቂዎች ደግሞ ከጓደኞቻቸው እና ከማህበረሰቡ አባላት ጋር መገናኘት ችለዋል።

"ከልባቸው ልጆች" የሆኑ ሁሉ በቂ ሁኔታ የተዝናኑ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ቀኑ በዙምባ ዳንስ እና በዮጋ ጀምሯል። ግዙፍ የሰሌዳ ጨዋታዎችን፣ ፊት መሳልን፣ የቴኳን ዶን ከምሥራቃ ኮልፋክሱ ቢዝነስ ከታይገር ኪም አካዳሚ፣ የግድግዳ ላይ ሥዕሎችን በቾክ እና የዴንቨር የእሳት አደጋ መከላከያ ጣቢያ 14 የእሳት አደጋ መኪና አዝናኙ ዝግጅት እንዲቀጥል አድርገውታል፣ እንዲሁም በጣም ለተጠበቁት ተሳታፊዎች፦ Liliana፣ Primrose፣ and Marigold -ዴንቨር ፍየሎችን ትወዳለች መድረኩን ምቹ አድርጓል። ልጆችም እና አዋቂዎችም ወደ ሶስቱም መቅረብ ችለዋል። የተሳታፊዎችን ጉልበት አጠንክሮ ማቆየት የምግብ ትራኮች እና የLittle Man አይስክሬም ሥራ ነበር። ይህም በእርግጠኝነት የፀሐዩን ኃይል ለማሸነፍ ረድቷል።



Las Dahlias - ሙሉ ለሙሉ የሴቶች የሆነ የMariachi ባንድ ወደ ቀኑ መገባደጃ ላይ ጣዕመ ዜማን አቅርቧል። ዝግጅቱ ሲጠናቀቅ መድረኩን ለThe Fax አጋርነት ሠራተኛ በመስጠት የሽልማት አሸናፊዎችን አሳውቀዋል። እነዚህም ሁለት የማህበረሰብ ልጆች አይፓድ ፕሮ ሲሸለሙ በርካታ ቤተሰቦች ከተሸለሙት መካከል የልጆች ሙዚየም አባልነት፣ የምግብ ስጦታ ቅርጫት እና የኮርስ ቢራ ፋብሪካን ጉብኝት ይገኙበታል። ላላሸነፉ፣ The Fax የልጆች ቦርሳዎችን፣ የአዋቂዎች የምስራቅ ኮልፋክስ የባህል ዲስትሪክት ምርቶችን እና የዴንቨር መካነ አራዊት እና የዴንቨር የተፈጥሮ እና ሳይንስ ሙዚየም ትኬቶችን በመስጠት ባዶ እጃቸውን እንዲሄዱ አላደረገም።


ዝግጅቱ ለነዋሪዎች፣ ለንግዶች እና ለምሥራቅ ኮልፋክስ የማህበረሰብ ድርጅቶች አስደናቂ ስኬት እና አስደሳች ነበር። ብዙዎች ገና ከወዲሁ የ2025 2ኛውን ዓመታዊ የምሥራቅ ኮልፋክስ ማህበረሰብ የመስክ ቀንን በጉጉት መጠባበቅ ጀምረዋል!







# የዴንቨር ፖሊስ እና የThe Fax መጠይቅ ስለደህንነትና ሰላም




Full Category Name: *Disorderly Conduct/Public Intoxication/Noise Complaints | **Violent Crimes (Assaults, Gun Violence) | ***Non-Violent Crimes (Graffiti, Vandalism, Prostitution)

## የዴንቨር ፖሊስ ዲፓርትመንት እና The Fax የምሥራቅ ኮልፋክስ ስለደህንነትና ሰላም መጠይቅ ያስሞላሉ

በ2023 የምሥራቅ ኮልፋክስ ንግዶች፣ ነዋሪዎች፣ ለትርፍ ያልተቋቋሙ አጋሮች እና የዴንቨር ፖሊስ ዲፓርትመንት (DPD) በምስራቅ ኮልፋክስ ላይ የሚከሰቱ ቀጣይ የወንጀል ክስተቶችን ለመፍታት በመደበኛነት ተሰብስበው ነበር። ይህ ሥራ የጋራ ደህንነታችንን ማሻሻልን ዓላማ አድርጎ በየሩብ ዓመቱ ስብሰባዎችን ማድረግ፣ ለአካባቢ ንግድ ቤቶች የደህንነት ማሻሻያዎች ላይ ኢንቨስት ማድረግን እና መረጃ መለዋወጥን የማድረግ ይዘት እና ቅርጽ እንዲኖረው ሆኗል።

በ2024 መጀመሪያ ላይ ይህ ሥራ ቀጥሏል ምክንያቱም በሚያሳዝን ሁኔታ ወንጀልም ቀጥሏልና። ዓመቱ የጀመረው የThe Fax አጋርነት ከDPD ጋር በመተባበር በፈጠረው ቀላል መጠይቅ ነው። ጽንሰ ሀሳቡ DPD ጥረቱን የማህበረሰቡን ፍላጎት በሚያንፀባርቅ መልኩ የህብረተሰቡን ዋና ዋና የወንጀል ስጋቶች መለየት ላይ እንዲያተኩር የነበረ ቢሆንም ህብረተሰቡ በእነዚህ አካባቢዎች ወንጀልን በመቀነስ ረገድ የDPDን ውጤታማነት የሚለካበት መንገድ እንዲኖረው ማድረግ ነበር። የኤሌክትሮኒካዊ መጠይቁ በምስራቅ ኮልፋክስ ማህበረሰቦች አራቱ ዋና ዋና ቋንቋዎች - እንግሊዘኛ፣ ስፓኒሽኛ፣ በርምኛ እና አማርኛ - ተተርጉሞ በፌብሯሪ እና ማርች መካከል በድምሩ ለ90 ምላሽ ሰጪዎች ተሰራጭቷል።

ከ23% በላይ ምላሽ ሰጪዎች የማህበረሰቡ ዋነኛ የወንጀል ስጋት የጥቃት/የግጭት ወንጀል እንደሆነ አስታውቀዋል። ለአደንዛዥ ዕፅ ተግባራት 18% የሚሆኑ መላሾች ድምጽ ሰጥተዋል፤ ከዚያም እንደ ሴተኛ አዳሪነት እና ውድመት ወይም ዝርፊያ ያሉ የጥቃት ያልሆኑ ወንጀሎች 12% ድምጽ ተሰጥቶባቸዋል።

በምሥራቅ ኮልፋክስ ብዙ ጊዜ ካሳለፉ እነዚህ ውጤቶች በምንም መልኩ አያስደንቁም፣ ሆኖም ግን ይህ መረጃ የአካባቢያችን የፖሊስ ኦፊሰሮችን በሥራቸው ቅድሚያ መስጠት ያለባቸውን በማመላከት እና በእነዚህ ጠቃሚ ቦታዎች ላይ ወንጀልን ለመቀነስ የሚረዳቸው ይሆናል። የዲስትሪክቱ ሁለት ኮማንደር አርጎን (Aragon) "መጠይቁን ያስሞላነው ማተኮር አለብን ብለን ያሰብነውን ብቻ ሳይሆን ህብረተሰቡ ትኩረት ሰጥተን እንድንሠራ የሚፈልገውን እንድናውቅ ፈለገን ነው" ሲሉ ገልጸዋል።

የዳሰሳ ጥናቱ ወይም የመጠይቁ ውጤቶች በቅርቡ የተመረጡትን የዴንቨር ከንቲባ ተቀዳሚ ትኩረቶችንም ያንፀባርቃሉ። ቅዳሜ ኤፕሪል 6 በHidden Brook በተካሄደው የማህበረሰብ ስብሰባ ከንቲባ ጆንስተን በ2024 መገባደጃ ላይ የጠመንጃ ጥቃትን በ20% መቀነስ የአስተዳደራቸው ግብ እንደሆነ ይፋ አድርገው ነበር። ከንቲባው እንዳስረዱት በሌሎች የአሜሪካ ከተሞች ተግባራዊ የተደረገና አወንታዊ ውጤት እያመጣ ያለውን ፕላስ ኔትዎርክ ምርመራዎች (Place Network Investigations) የተባለ ስትራቴጂን በመጠቀም አስተዳደራቸው እና DPD ተባብረው ይህንን የጠመንጃ ጥቃትን ለመቀነስ እና አሁን ላይ እየተሰራ ነው ብለዋል።

የከንቲባው ግብ እና የማህበረሰብ መጠይቁ ውጤቶች ለምሥራቅ ኮልፋክስ ማህበረሰብ የጸጥታ መሻሻል ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ አጉልተው ያሳያሉ። ነገር ግን መጠይቆች እና ግቦች ፋይዳ የሚኖራቸው የተሻሻሉ ውጤቶችን ካስገኙ ብቻ ነው። በዚህ ምክንያት፣ ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች፣ ቢዝነሶች፣ ነዋሪዎች እና የከተማችን አስተዳደር ለውጡን ለማምጣት እና ሁላችንም የምንፈልገውን ደህንነቱ የተጠበቀ ሰላማዊ አካባቢን ለመፍጠር ትብብራችንን መቀጠል ያለባት ይመስለናል። ይህንን ለማረጋገጥ ደግሞ The Fax እና DPD በ2025 መጀመሪያ ላይ ቀጣይ መጠይቅን ለመበተን አቅደናል - ይከታተሉን!

ጁን 2024






## የምሥራቅ ኮልፋክስ ቢዝነስ ፒን ፕሮግራም

ነዋሪዎችን እና አነስተኛ የንግድ ተቋሞችን ለማክበር በምሥራቅ ኮልፋክስ የባህል ዲስትሪክት ተልእኮ ላይ በመገንባት፣ የአካባቢ ንግዶችን በማህበረሰቡ ውስጥ እና ከዚያም ባለፈ ለማስተዋወቅ The Fax አዲስ ፕሮግራምን እያስተዋወቀ ነው።

**ምንድነው?**
የምሥራቅ ኮልፋክስ የባህል ዲስትሪክት ዓርማን እና ወደ ባህላዊ ዲስትሪክቱ ድረ ገጽ ጋር የሚያገናኝ የQR ኮድን የያዘ ልብስ ላይ የሚሰካ ፒን ነው።

**ምን ያደርጋል?**
በመጀመሪያ ምሥራቅ ኮልፋክስን በቀላል ነገር ግን በሚታይ መንገድ ያስተዋውቃል። ሁለተኛም፣ ያ ፒን ያለው ማንም ሰው ስለ ምሥራቅ ኮልፋክስ እንደሚያውቅ ምልክት ሆኖ ያገለግላል። ምሥራቅ ኮልፋክስ ምን ያህል ምርጥ እንደሆነ ማወቅ ብቻ ሳይሆን ከአካባቢው ንግዶች ልዩ ቅናሾችን ያገኛሉ።

**ለምን ፒን?**
ትንሽ ነገር ግን የሚታይ፣ ጠንካራ እና ለመያዝ ቀላል የሆነ ነገር ፈልገን ነው።

**ስለ ምን ዓይነት ቅናሾች ነው ያወራነው?**
እያንዳንዱ ንግድ የተለየ ነው፣ ነገር ግን በግዢዎች ላይ እስከ 15% ለማዳን፣ በቅርብ ጊዜ ተመራጭዎ ከሚያደርጉት አንድ ምግብ ቤት ውስጥ ነጻ መጠጥ ወይም መተግበሪያ ለማግኘት፣ ወይም ነጻ የፀጉር ቁርጥ ለማግኘት ይችላሉ!

**መቼ ይጀምራል?**
ተጀምሯል፣ ስለዚህ እንዳያመልጥዎ! በሳመሩ ወቅት አዳዲስ ንግዶችን እንጨምራለን። ስለዚህ አሁን የሚፈልጉት ቅናሽ ባያገኙም ፒኑን ይያዙ እና ተመልሰው ማየትዎን (ቼክ ማድረግዎን) ይቀጥሉ!

## ለራስዎ ፒን ይፈልጋሉ?

ወደ እኛ ቢሮ፣ እዚህ በተዘረዘሩት ተሳታፊ መደብሮች ወደ አንዱ ብቅ ይበሉ ወይም አንድ ለማንሳት እና የQR ኮዱን ስካን አድርገው የዘመነውን የተሳታፊ ንግዶች ዝርዝርን ይመልከቱ!

**የሚሳተፉ ንግዶች**

- Quince Coffee House
- El Tamarindo (303) 320-5490
- Tiger Kim's Tae Kwon Do Tang Soo Do Academy
- Lucy Ethiopian Restaurant
- Carniceria Jerezana
- Famous Buffalo Wings & Things
- El Chalate Salvadorian & Mexican Food
- オタク
- Krizpy Fadez Barbershop
- East Fax Tap
- Sarahi's Kitchen Fresh Mexican Food
- The Speakeasy Hair Co

**... እና ሌሎች ወደፊት ይጨመራሉ!**

the fax

The Fax Partnership
6740 E. Colfax Ave.
Denver, CO 80220









## Want to learn more about what's next, or to get involved?

Website: thefaxdenver.com
Email: info@thefaxdenver.com
Social: @faxpartnership
@partnershipfax

## Just THE FAX ጁን 2024

**ስለሚቀጥሉት ነገሮች የበለጠ ማወቅ ወይም ለመሳተፍ ይፈልጋሉ?
የፋክስ የነዋሪዎች ድጋፍ ቢሮ፡- የማህበረሰቡን ፍላጎቶች ለማሟላት
የ2024 1ኛ ግማሽ ተጽዕኖ/ክንውኖች**



- በድምሩ $109,883 የታክስ ተመላሽ ገንዘብን ያስገኙ 133 የታክስ ሠነዶችን የመሙላት እገዛ ተሰጥቷል።
- 625 ቤተሰቦች የምግብ እደላ ፕሮግራም ውስጥ ተጠቃሚ ሆነዋል።
- 662 ልጆች ዳይፐር ተቀብለዋል።
- ለ155 ደንበኞች መረጃዎችን የማቅረብ አገልግሎት ተሰጥቷል።
- 21 ደንበኞች ማመልከቻዎችን የመሙላት እገዛን አግኝተዋል።
- ከ200 በላይ ነዋሪዎች የበጋ የመክፈቻ (Summer Kick-Off) ትርኢት ላይ ተገኝተዋል።

## የቀን መቁጠሪያዎ ላይ ምልክት ያድርጉ

**ወደ ትምህርት ቤት የመመለሻ አውደ
ርዕይ
ኦገስት 1፣ ከ5-7 ፒ.ኤም.
በThe Fax አጋርነት ቢሮ
6740 East Colfax Avenue**

## 2ኛ ዓመታዊ የፋክስ ገንዘብ ማሰባሰብያ

**የThe Faxን 20ኛ ዓመት ለማክበር ይምጡ ይቀላቀሉን!**
ሐሙስ ሴፕቴምበር 19
ከቀኑ 5:30-7:30 ፒ.ኤም.
መስተንግዶ በEast Fax Tap
8001 East Colfax Ave.

ቲኬቶችዎን አሁን ለመግዛት የQR ኮድን ስካን ያድርጉ!